# የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር ማቋቋሚያ ቻርተርን ለማሻሻል የቀረበ የማሻሻያ ኃሳብ/ሀተታ

ሰኔ 2009ዓ.ም

- ማስታወሻ

  እባክዎ ይህን ሀተታ ዘምክንያት ሲያነቡ ከአዋጁ ጋር እያገናዘቡ ያንብቡት፡፡ በመጨረሻ በዚህ ሰነድ መሰረት ተስተካክሎ የቀረበውን ረቂቅ ቻርተር ያንብቡት፡፡

## መግቢያ

የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር በመንግስት ፈቃድ እና መንግስት አጽድቆ በሰጠው ቻርተር መሰረት በ1927 ዓ.ም ተመስርቶ በተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋ ጦርነትን ጨምሮ አደጋ ለደረሰባቸው እና ለአደጋ ለተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎች አስፈላጊውን የሰብዓዊ ድጋፍ ሲያደርግ የቆየ ማኅበር ነው፡፡ ማኅበሩ የሚተዳደርበትን ቻርተር በየጊዜው ከሚኖረው የሰብዓዊ ድጋፍ፣ ከሀገር አቀፍ እና አለም ዓቀፍ ሁኔታ አንጻር እንዲሻሻል በማድረግ የሰብዓዊ አገልግሎት አድማሱን በማስፋት አስፈላጊውን ድጋፍ በየጊዜው እና በብቃት ለማድረስ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

አሁንም ማህበሩ የሚተዳደርበትን ቻርተር ከነባራዊው ሀገራዊ እና አለምዓቀፋዊ ሁኔታ ጋር ተጣጥሞ እንዲሔድ እና ማኅበሩ ራሱን ለመቻል የሚያደርገው ጥረት ተሳክቶ በራሱ አቅም አደጋ የደረሰብቸውንና ለአደጋ የተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎችን በራሱ አቅም ድጋፍ ለማድረስ በሚችልበት ደረጃ ላይ እንዲደርስ ቻርተሩን ማሻሻል በማስፈለጉ እና ቻርተሩን ለማሻሻል የተቋቋመው ኮሚቴ ያቀረበውን ረቂቅ ጥር 17 ቀን 2007 ዓ.ም የሀገር አቀፉ ጠቅላላ ጉባኤ ተቀብሎ በማጽደቅ ረቂቁ ለመንግስት ቀርቦ እንዲጸድቅ ወስኗል፡፡

የሀገር አቀፍ ጠቅላላ ጉባኤው ከሰጠው ውሳኔ በተጨማሪም በቻርተሩ አንቀጽ 16/9 መሰረት በአለም አቀፉ ቀይ መስቀል ኮሚቴ እና በአለም አቀፉ ቀይ መስቀል እና ቀይ ጨረቃ ፌዴሬሽን የብሔራዊ ማኅበራትን ቻርተር ለመመርመር ለተቋቋመው የጋራ ኮሚቴ የማኅበሩ ረቂቅ ቻርተር ተልኮ ከኮሚቴው የቀረበው አስተያየት በዚህ ረቂቅ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የማኅበሩ ባለድርሻ አካላት ከሆኑት ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እና ከፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ የተሰጡ አስተያየቶች እና ማስተካከያዎች በቻርተሩ ረቂቅ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

በመጨረሻም ይህ ረቂቅ ቻርተር የመጨረሻ ቅርጹን የያዘው የማኅበሩ ሀገር አቀፍ ጠቅላላ ጉባኤ ቻርተሩ እንዲሻሻል የሰጠውን ውሳኔ መሰረት በማድረግ እና የማህበሩ ባለድርሻ አካላት በተለይም የፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ የህግ ቅርጹን እንዲጠብቅ፣ የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ማኅበሩ በጠየቀው ከታክስ እና ቀረጥ ነጻ መብት ላይ ማስተካከያ አድርጎበት እና ስምምነቱን ገልጾበት ነው፡፡ በመሆኑም ቻርተሩ ውስጥ የተደረጉትን ዋና ዋና ማሻሻያዎች እና ማብራሪያቸው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## በቻርተሩ ውስጥ ማሻሻያ የተደረገባቸው ነጥቦች  ዝርዝር

## የቻርተሩ መግቢያ

በቻርተሩ መግቢያ የመጀመሪያው አንቀጽ ላይ ቀይ መስቀል የአለም አቀፉ ቀይ መስቀል እና ቀይ ጨረቃ እንቅስቃሴ አካል መሆኑ ስለ ቀይ መስቀል እና ቀይ ጨረቃ እንቅስቃሴ የተሻለ ግንዛቤ ስለሚፈጥር እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

“የአለም አቀፍ ቀይ መስቀል እና ቀይ ጨረቃ እንቅስቃሴ አካል የሆነው ቀይ መስቀል በዘር፣ በቀለም፣ በዜግነት፣ በጾታ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት ወይም በማናቸውም ሌላ ሁኔታ ልዩነት ሳያደርግ በጦር ሜዳ ለሚቆስሉና ለሚጐዱ በአጠቃላይ በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎች ለሚጠቁ ሰዎች ተፈላጊውን ሰብአዊ ዕርዳታ በፍጥነት የሚሰጥና በሰዎች ዘንድ መግባባት፣ መተባበር፣ ወዳጅነትና ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን የሚጥር ዓለምአቀፍ እንቅስቃሴ በመሆኑ፣”

በቻርተሩ መግቢያ ሁለተኛው አንቀጽ ላይ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር መቼ እንደተመሰረተ እና የአለም አቀፉ ቀይ መስቀል እና ቀይ ጨረቃ እንቅስቃሴ አካል የሆነው መቼ እንደሆነ መጥቀሱ ስለማኅበሩ ታሪክ እና እንቅስቃሴ የተሻለ ግንዛቤ እንደሚፈጥር ስለታመነበት እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

“የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር በ1927 ዓ.ም. ተመስርቶ በዚሁ አመት በአለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ እውቅና አግኝቶ የአለም አቀፍ ቀይ መስቀል እና ቀይ ጨረቃ ፌዴሬሽን  አባል በመሆን በመንግሥትና በኅብረተሰቡ በተለይም በአባላቱ ጠንካራ ድጋፍ በመዋቅር ስፋትም ሆነ በአገልግሎት አቅርቦት እያደገ መምጣቱን በመገንዘብ፣”

በመግቢያው አምስተኛው አንቀጽ ላይ ያለው ሓሳብ አሁን ቻርተሩን ለማሻሻል ለተፈለገበት አላማ የማይውል እና ቻርተሩን ማሻሻል በተፈለገበት አላማ  መተካት ስላለበት እንደሚከተለው እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡

‹‹ማኅበሩ አላማውንና ተልዕኮውን ለማሳካት እንዲሁም የሚጠበቅበትን ሰብዓዊ አገልግሎት በብቃት ለማከናወን እና ራሱን ለመቻል የተለያዩ የገቢ ምንጮችን ለማፍራት የሚያደርገውን ጥረት ከግቡ ለማድረስ እና እየተገበረው ያለውን የለውጥ ሂደት በስኬት ለመፈጸም ቀልጣፋ፣ ግልጽነት እና ተጠያቂነትን የሚያሰፍን አወቃቀር እና አደረጃጀት መከተል ያለበት በመሆኑ››

## በአንቀጽ 2 ስር የተደረጉ ማሻሻያዎች

1. በንዑስ አንቀጽ 2.2 “ቀበሌ” የሚለው በአጠቃቀም ላይ የሚፈጥረው አሻሚ ነገር የሌለ በመሆኑ ለቃሉ ትርጉም ማስቀመጡ እንዲቀር ሆኗል፡፡

2. በንዑስ አንቀጽ 2.3 የቀይ መስቀል ወጣት የሚለው ትርጉም የማኅበሩን የቀይ መስቀል ወጣቶችን ፖሊሲ እና በእንቅስቃሴው ውስጥ ያሉ አካላት የሚጠቀሙበትን አካሄድ መከተል ያለበት በመሆኑ የቀይ መስቀል ወጣት ማለት ዕድሜው ከ15 ዓመት እስከ 30 ዓመት ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር ወጣት አባል ነው በሚል ተስተካክሎ ወደ 2.2 ተሸጋሽጓል፡፡

3. የአለም አቀፉ ቀይ መስቀል እና ቀይ ጨረቃ እንስቃሴ በተለምዶ እንቅስቃሴው እየተባለ የሚጠራው በቻርተሩ ውስጥ በብዛት የሚጠቀስ በመሆኑ እንቅስቃሴው ለሚለው ቃል ትርጉም መስጠት በማስፈለጉ በረቂቅ ቻርተሩ አንቀጽ 2.3 ስር "እንቅስቃሴ" ወይም "እንቅስቃሴው" ማለት ብሔራዊ የቀይ መስቀል እና ቀይ ጨረቃ ማኅበራትን፤ ዓለም አቀፉን የቀይ መስቀል ኮሚቴ እና ዓለም አቀፉን የቀይ መስቀል እና ቀይ ጨረቃ ፌዴሬሽንን በአባልነት የያዘ ጥምረት ነው ተብሎ ተተርጉሟል፡፡

4. በጎ ፈቃደኛ የሚለው ሀረግ በቻርተሩ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ ቢሆንም ትርጉም ያልተሰጠው በመሆኑ አጠቃቀሙ ላይ ችግር እንደሚፈጥር ግንዛቤ በመወሰዱ አንቀጽ 2.4 ስር ትርጉሙን ከእንቅስቃሴው እና ከማኅበሩ የአባላት ፖሊሲ ላይ በመውሰድ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

5. ከማኅበሩ የአባልነት አይነቶች አንዱ የድርጅት አባል በመሆኑና የዚህንም አባልነት አይነት እና ይዘት በትርጉም ማስቀመጥ በማስፈለጉ በአንቀጽ 2.6 “የድርጅት አባል” ትርጉም እንዲሰጠው ተደርጓል፡፡

6. ሰው የሚለው ቃል የተፈጥሮ ሰውን እና በህግ የሰውነት መብት የተሰጠውን አካል እንደሚወክል በህግ ትርጉም ያለው በመሆኑ በቻርተሩ ውስጥ የቃሉ አጠቃቀም ወጥ ትርጉም ያለው እንዲሆን ይህን በቻርተሩ አንቀጽ 2.7 ስር እንዲካተት ተደርጓል፡፡

7. በህጉ ውስጥ በወንድ ጾታ የተጻፈው ለሴት ጾታም እንደሚያገለግል ለማሳሰብ በአንቀጽ 2.8 ይሄው ተካቷል፡፡

**አንቀጽ 3** በዚህ አንቀጽ ስለማኅበሩ ህጋዊ ሰውነት እና ተግባሩን ስለሚያከናውንበት የህግ መሰረት የተገለጸውን በሁለት ንዑስ አንቀጽ በመክፈል በንዑስ አንቀጽ 1 ስለማኅበሩ ባህሪ በንዑስ አንቀጽ 2 ስራውን ስለሚያከናውንበት የህግ መሰረት እንዲካተት ተደርጓል፡፡ በይዘቱም ላይ ማኅበሩ የእንቅስቃሴው አካል በመሆኑ በዚያ በኩል ያሉበት ግዴታዎች እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

**አንቀጽ 4** በዚህ አንቀጽ ስለ ማኅበሩ አርማ እና ስለ አጠቀቀሙ የተገለጸውን በሁለት አንቀጽ በመክፈል በአንቀጽ 4 ማኅበሩ የሚጠቀምበትን አርማ በተመለከተ ይህም በነጭ መደብ ላይ በጉልህ የሚታይ ቀይ መስቀል መሆኑ እና በነጭ መደብ ላይ ቀይ መስቀል ብቻ ከሆነ አርማው ለከለላነት ብቻ ሲያገለግል ጥቅም ላይ የሚውል በመሆኑ እ.አ.አ. በ1991 በእንቅስቃሴው አካላት የጸደቀውን የአርማ አጠቃቀም በመከተል በአርማው ላይ የማኅበሩ ስም በሙሉ ወይም በአጭር ጽህፈት አብሮ የሚካተት መሆኑን በሚገልጽ መልኩ እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ አዲስ አንቀጽ 5 ተጨምሮ ስለ አርማው አጠቃቀም እና ማኅበሩ አርማው በተገቢው ጥቅም ላይ እንዲውል ስላለበት ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ በሚከተለው መልኩ ተካቷል፡፡

"5. <u>ስለዓርማው አጠቃቀም</u>

1/ የዓርማው አጠቃቀም በጄኔቫ ስምምነቶች፣ ብሔራዊ ማኅበራት በአርማው የሚጠቀሙበትን ሁኔታ በሚመለከት በ1984 ዓ.ም በእንቅስቃሴው አለምአቀፍ ስብሰባ በተደነገገው ደንብ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው የሃገሪቱ ህጎች መሠረት የተወሰነ ይሆናል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንም ሰው ያለ ማኅበሩ ፈቃድ እና እውቅና አርማውን በማንኛውም ሁኔታ መጠቀም አይችልም፡፡

3/ የማኅበሩ አባላት፣ ሰራተኞቹ እንዲሁም የበጎ ፈቃድ አገልጋዮች አርማውን ስለሚጠቀሙበት ሁኔታ እና ለአርማው መደረግ ስላለበት ጥበቃ የሚወስን የጄኔቫ ስምምነቶችን፣ ተጨማሪ ፕሮቶኮሎች እና ብሔራዊ ማኅበራት በአርማው የሚጠቀሙበትን ሁኔታ በሚመለከት በ1984 ዓ.ም በእንቅስቃሴው ዓለም ዓቀፍ ስብሰባ በተደነገገው ደንብ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የሀገሪቱ ሕጎችን መሠረት ያደረገ የውስጥ ደንብ ያወጣል፡፡

4/ ማኅበሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (3) በተገለጸው መሰረት አግባብነት ካላቸው የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር አርማው በሀገር ውስጥ ለትክክለኛ ዓላማ መዋሉን ይከታተላል፡፡"

**አንቀጽ 5** የማኅበሩ መሠረታዊ መርሆች እንዲሁ ተዘርዝረው መታለፉ ስለ መርሆቹ በቂ ግንዛቤ ስለማይፈጥር የእያንዳንዱ መርህ በእንቅስቃሴው አካላት መተዳደሪያ ደንብ ላይ ከተሰጠው ትርጉም/ማብራሪያ ጋር አብሮ ቢጻፍ መርሆቹን በቀላሉ ለመረዳትና ተግባር ላይ

ለማዋል እንደሚረዳ አስፈላጊነቱ ስለታመነበት የቁጥር ማስተካከያ ተደርጎ በአንቀጽ 6 ስር እንዲካተት ተደርጓል፡፡

**አንቀጽ** 6 ማኅበሩ ከተቋቋመበት መርኀ አንጻር አደጋ ከመድረሱ በፊት፣ ሲደርስ እና አደጋው ካለፈ በኂላ ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ እና ጉዳት የደረሰባቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ከመርዳት አልፎም ለአደጋ የማይበገር ማኅበረሰብ እንዲኖር መጣር ያለበት በመሆኑ ከዚህ አንጻር የማኅበሩ አላማ በአንቀጽ 7 ስር እንደሚከተለው ተቀርጿል፡፡

“7. <u>ዓላማ</u>

የማኅበሩ ዓላማ የጄኔቫ ስምምነቶችንና በዚህ ቻርተር አዋጅ አንቀጽ 6 የተመለከቱትን መሠረታዊ መርሆች በመከተል የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፤

1/ በሰው ሰራሽ እና በተፈጥሮ አደጋ ግጭቶችን ጨምሮ በሰው ህይወትና ጤና ላይ የሚደርሰውን ስቃይ እና መከራ ማቃለል፣ የተጠፋፉ ቤተሰቦችን ማገናኘት፣ የአደጋ ተጎጂዎች ከጉዳቱ በፍጥነት እንዲያገግሙ የማድረግ፤

2/ በተፈጥሮ አደጋ ግጭቶችን ጨምሮ በሰው ጤናና ህይወት ላይ አደጋ እንዳይደርስ መከላከል፣ የህብረተሰቡን አደጋ የመቋቋም አቅም የማዳበር፤

3/ ሰብዓዊነት፣ በጎ ፈቃደኝነት እና የሰው ልጆች ሰላም እንዲሰፍን የመስራት፡፡”

**የተጨመሩ አዲስ አንቀጾች**

ማኅበሩ በመንግስት ፈቃድ የሚቋቋም ስራውን በሰብዓዊ ተግባራት የመንግስት አጋዥ በመሆን የሚሰራ ቢሆንም የአሰራር ነጻነት ያለው እና ከመንግስትም ሆነ ከሶስተኛ አካላት ጋር የሚያደርገው ግንኙነት የማኅበሩን መርሆች መጠበቅ ያለበት በመሆኑ ይህን በግልጽ ለማመላከት ሶስት ተጨማሪ አንቀጾች በሚተለው መልኩ ተጨምረዋል፡፡

“8. <u>ከመንግስት ጋር ስላለው ግንኙነት</u>

1/ ማኅበሩ የተቋቋመለትን ዓላማ እና መሠረታዊ መርሆችን በመጠበቅ በሰብዓዊ ተግባራት የመንግስት አጋዥ ነው፡፡

2/ መንግስት ማኅበሩ የተቋቋመለትን ዓላማ እንዲያሳካ እና በዚህ ቻርተር የተዘረዘሩትን ተግባራት እንዲፈጽም አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

3/ ማኅበሩ ከመንግስት አካላት ጋር ስለማህበራዊ አገልግሎት አሰጣጥ የሚያደርጋቸው ስምምነቶች በጽሁፍ መሆን አለባቸው፡፡

9. <u>ተቋማዊ ነጻነት</u>

1/ ማኅበሩ የተቋቋመለትን ዓላማ ሲያከናውን ተቋማዊ ነጻነት አለው፡፡

2/ መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ከማኅበሩ ጋር የሚያደርጓቸው ማናቸውም ግንኙነቶች ከማኅበሩ መርሆች ጋር የሚጻረሩ መሆን የለባቸውም፡፡

10. <u>ከሌሎች አካላት ጋር ስላለው ግንኙነት</u>

1/ ማኅበሩ ከሌሎች የእንቅስቃሴው አካላት ጋር ስላለው ግንኙነት በእንቅስቃሴው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 3 እና 4 የተቀመጡትን ድንጋጌዎች እንዲሁም በዓለም ቀይ መስቀል እና ቀይ ጨረቃ ፌዴሬሽን መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 8 ላይ የተጠቀሱትን ግዴታዎች ያከብራል፡፡

2/ ማኅበሩ የተቋቋመለትን ዓላማ ለማሳካት መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት፣ ህዝባዊ ማኅበራት እና አግባብነት ካላቸው የግል ድርጅቶች ጋር ሊሰራ ይችላል፡፡"

## አንቀጽ 7 ስር የተደረጉ ማሻሻያዎች

ከላይ በተጨመሩ አዳዲስ አንቀጾች ምክንያት ይህ አንቀጽ ወደ አንቀጽ 11 የተስተካከለ ሲሆን በዚህ አንቀጽ ውስጥ ከተካተቱት ውስጥ:-

1. ማኅበሩ ከተቋቋመበት አላማ እና ከእንቅስቃሴው ደንቦች አንጻር ማኅበሩ ድጋፍ የሚያደርግበትን ሁኔታ ግልጽ ማድረግ በማስፈለጉ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ ተጨምሯል፡፡ "11.1 በትጥቅ ግጭት፡ በውስጥ አለመረጋጋቶችና ውጥረቶች እንዲሁም በድንገተኛ እና በሌሎች አደጋዎች ውስጥ የሚገኙ ተጋላጭ ሰዎችን እና የህብረተሰብ ክፍሎችን ሁኔታ ማሻሻል፡"
2. በአንቀጽ 7.3 ስር ማኅበሩ በሰብዓዊ ተግባራት የመንግስት አጋዥ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚከተለው ተጨማሪ ኃሳብ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ ‹‹በአደጋ ተጋላጭነት ምላሾች ላይ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ፣ ከመንግስት ጋሩ በመተባበር የአደጋ ተጋላጭነትን መቀነስ እና የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ››
3. በአንቀጽ 7.6 ለአደጋ ተጋላጭ ከሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ አካል ጉዳተኞች እና አረጋውያን የሚካተቱ በመሆናቸው ይሄው እንዲገባ ተደርጓል፡፡
4. በጄነቫ ስምምነቶችም ሆነ በእንቅስቃሴው ህጎች የታወቀው አንዱ የማህበሩ ተግባር የተጠፋፉ ቤተሰቦችን ማገናኘት በመሆኑና ይህንንም ተግባሩን በቻርተሩ ውስጥ ማስገባት በማስፈለጉ በአዲስ ንዑስ አንቀጽ 11.9 ሆኖ ተካቷል፡፡
5. ከአንቀጽ 7.14-16 ያሉት በአንድ ሐሳብ ሊጠቃለሉ የሚችሉ ኃሳቦች በመሆናቸው በአንድ ንዑስ አንቀጽ እንዲጠቃለሉ ተደርጓል፡፡

**አንቀጽ** 10/3 የክብር አባልነት የሚሰጠው ከቀይ መስቀል ስራዎች ጋር በተያያዘ ለሚፈጸም ከፍተኛ የሰብዓዊ ተግባር መሆኑ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ የቁጥር መዛባቱም እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡

**አንቀጽ** 11/4/ የቦርድ የአገልግሎት ዘመንን የሚመለከት በመሆኑ ይህ ንዑስ አንቀጽ በአንቀጽ 25.2 ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

አንቀጽ 12/1/ሀ አባልነት የሚሠረዝበትና የሚታደስበትን ሁኔታ በተመለከተ በነባሩ ቻርተር ላይ የዓመቱን የአባልነት ክፍያ ለሁለት ተከታታይ ዓመታት ሲቋረጥ አባልነት ይሰረዛል ተብሎ የተቀመጠው የአባልነት ክፍያ በተከታታይ ለሚከፍሉ ለመደበኛ አባላት ብቻ ስለሚያገለግል በዚሁ መልኩ ተሻሽሏል፡፡

በተጨማሪ በአንቀጽ 12.3 መሰረታዊ መርሆች በአባሉ ተጥሰዋል ሲባል ምን ተግባራትን ሲፈጽም እንደሆነ ዘርዘር ተደርጎ በአንቀጽ 16.3 ተቀምጧል፡፡

**አንቀጽ** 12/4/ ማንኛውም አባል ከአባልነቱ ሲሰረዝ የተሰናበተበትን ምክንያት የሚገልጽ የጽሁፍ ማስረጃ እንዲሰጠው ይደረጋል፡፡ ማኅበሩ የአባላት እና የበጎ ፈቃደኞች እንደመሆኑ እንዲሁም በየደረጃው በሚገኘው የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ወቅት ቀርቦ ጉባኤው እንዲያውቀው መደረጉ አንድም የአባላቱ ወኪል የሆነው ጠቅላላ ጉባኤ ስለ አባሉ እጣ ፈንታ እንዲያውቅ የሚያደርገው ሲሆን በሌላ በኩልም በአባላት አያያዝ ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት አመራር እንዲሰጥ ስለሚረዳው ይህ በአንቀጹ ውስጥ 16.4 ሆኖ እንዲገባ ተደርጓል፡፡

## ክፍል ሶስት

በዚህ ክፍል ስር የማኅበሩ አደረጃጀት የሚለው ‹‹የማኅበሩ አደረጃጀት እና አወቃቀር›› በሚል እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡

**አንቀጽ** 13 የበላይ ጠባቂ የሚለው የሀገሪቱ ፕሬዚደንት ነው የሚለው ብቻ እንዲሆን ተደርጎ ለማኅበሩ የሚሰጠው ድጋፍ በንዑስ ቁጥር 2 እንዲገባ ተደርጓል፡፡ አንቀጹም አንቀጽ 17 ተብሎ ተስተካክሏል፡፡

## የማኅበሩ አደረጃጀት

የማኅበሩ አደረጃጀት አዲስ አንቀጽ 18 ሆኖ እንዲገባ የተደረገ ሲሆን የብሔራዊ፣ የክልል፣ የዞን የልዩ ወረዳ እና የወረዳ አደረጃጀቶች ያላቸውን ኃላፊነት እና የግንኙነት መስመር በግልጽ እንዲያሳይ ተደርጓል፡፡

አንቀጽ 14/2/ በማኅበሩ አወቃቀር ላይ የተደረገው ለውጥ ልዩ ወረዳ የሚለው አወቃቀር በቻርተሩ እውቅና እንዲያገኝ መደረጉ ነው፡፡

**አንቀጽ 15 ላይ የተደረጉ ማሻሻያዎች፡-**

ይህ አንቀጽ አንቀጽ 20 ተብሎ ተስተካክሎ የሚከተሉት ማሻሻያዎች ተደርገዋል፡-

1. በአንቀጽ 20.3 የአባላትን ተሳትፎ ለማስፋት በ100,000 አባላት በአንድ ተጨማሪ አባል እንዲወከል ተደርጓል፡፡
2. በአንቀጽ 20.4/ሐ እና ሠ ከማኅበሩ ስራ ጋር ተያያዥነት ስላላቸው የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና የትምህርት ሚኒስቴር በጠቅላላ ጉባኤ አባልነት እንዲካተቱ ተደርጓል በአንቀጽ 20.4. ረ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን የሚለው አሁን ባለው ስም የብሔራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን በሚል ተስተካክሎ እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡
3. በአንቀጽ 20.7 የቀይ መስቀል ወጣቶችን ወደ አመራርነት ለማምጣት 3 የቀይ መስቀል ወጣቶች በአባልነት እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡
4. በአንቀጽ 20.9 በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ይጠሩ የነበረው ተጨማሪ 30 አባላት በሀገር አቀፍ ቦርዱ እንዲጠሩ ተደርጓል፡፡
5. በአንቀጽ 20.10 ተመራጭ የሆኑ የጠቅላላ ጉባኤ አባላት የአገልግሎት ዘመን ለአራት ዓመታት ሆኖ ከሁለት ተከታታይ ምርጫ በላይ እንዳይሆን ተደርጓል፡፡

**አንቀጽ 16/1/** የአስተዳደር ቦርድ አባላት የሚመረጡት ከማኅበሩ አባላት መሆኑ የታወቀ በመሆኑ የጠቅላላ ጉባኤው ስልጣንና ተግባር ውስጥ ይህን መጻፍ አስፈላጊ ባለመሆኑ በቀላሉ የአስተዳደር ቦርድ አባላትን መምረጥ ብቻ ተብሎ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡

አንቀጽ 16/3 በዚህ አንቀጽ የጠቅላላ ጉባኤው ስልጣንና ተግባር በጀት እና እቅድ ከማጽደቅ አንጻር ጥቅል በጀት እና እቅድ እንዲያጸድቅ ሆኖ ዝርዝር በጀት እና እቅድ አስተዳደር ቦርዱ እንዲያጸድቅ ተደርጓል፡፡ አንቀጹም 21/4 ተብሎ ተስተካክሏል፡፡ በተጨማሪነትም በአዲስ ንዑስ አንቀጽ 21/11 የራሱን የስብሰባ ስነ ስርዓት እና ስለ አስተዳደር ቦርዶች ምርጫ ደንብ ማጽደቅ አንዱ ተግባሩ ሆኖ ተቀምጧል፡፡

**አንቀጽ 17/ሐ/** የጠቅላላ ጉባኤውን ልዩ ስብሰባ ለመጥራት የተቀመጠው ስርዓት ውስብስብ በመሆኑ የበለጠ ቀለል ለማድረግ በአንቀጽ 22/3/ሐ ስር የክልል ቦርዶች የጠቅላላ ጉባኤ እንዲጠራ ስለሚጠይቁበት ሁኔታ ተካቷል፡፡

አንቀጽ 18/2 ስር በዚህ ቻርተር በአንቀጽ 30 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚለው አገላለጽ በቻርተሩ በልዩ ሁኔታ የተቀመጡ አስገዳጅ ልዩ ድንጋጌዎችን ለማመላከት በመሆኑ አጻጻፉ ‹በዚህ ቻርተር በተለየ ሁኔታ ካልተገለጸ በቀር› በሚል እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡

የተፈጠረው የቁጥር መዛነፍም እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም በዚሁ ንዑስ አንቀጽ ‹ለ› ስር ውሳኔ የሚወሰነው በድምፅ ብልጫ ይሆናል የሚለውን የበለጠ ገላጭ ለማድረግ ውሳኔ የሚወሰነው በስብሰባ ተገኝተው ደምጽ በሰጡ አባላት የድምጽ ብልጫ እንደሚሆን በሚያመለክት መልኩ እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡

**አንቀጽ 18/5/** የጠቅላላ ጉባኤ ዘጋቢ አንድ መሆኑ ቀርቶ እየተሰራበት ባለው ሶስት እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

በአንቀጽ 19 ስር የተካተቱ ማሻሻያዎች

ይህ አንቀጽ ከላይ በተደረጉት ጭማሪዎች አንቀጽ 24 ሆኖ የተስተካከለና ስያሜውም የብሔራዊ አስተዳደር ቦርድ የተባለ ሲሆን የሚከተሉት ማሻሻያዎች ተጨምረዋል፡-

1. ከዘጠኙ የቦርድ አባላት አንዱ ከወጣቶች የሚመረጥ ተወካይ እንዲሆን መደረጉ፤
2. የአስተዳደር ቦርድ አባላት ምርጫ የጾታ፣ የልምድ እና የሙያ ስብጥርን መሰረት ማድረጉ፤
3. በአስተዳደር ቦርድ አባላት ምርጫ ላይ የቦርድ አባላት የሚመረጡት በጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ ላይ ከተገኙት አባላት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ለማኅበሩ ጥሩ የሚሰሩ መሆናቸው የታመነባቸው እና ለማገልገልም ፈቃደኝነታቸውን ያረጋገጡ አባላት ነገር ግን በተለየ ምክንያት በስብሰባው ሳይገኙ የቀሩ አባላትን በቦርድ አባልነት መምረጥ እንዲቻል መደረጉ፤
4. የአስተዳደር ቦርድ አባላቱ ከጥቅም ግጭት ነጻ መሆን እንዳለባቸው መገለጹ፤
5. የአስተዳደር ቦርድ አባላቱ የማኅበሩን ጥቅም ማስቀደም ያለባቸው መሆኑ፤ በፖለቲካ ድርጅት ወይም በመንግስት መዋቅር ውስጥ ከፍተኛ ኃላፊነት ከተሰጣቸው ይህ ኃላፊነታቸው ከማኅበሩ ጥቅም ጋር እንደማይጋጭ ማረጋገጫ መስጠት ያለባቸው ስለመሆኑ ወይም የቦርድ ኃላፊነታቸውን መልቀቅ እንዳለባቸው መካተቱ፤
6. የፖለቲካ ኃላፊዎች ወይም የመንግስት ከፍተኛ ኃላፊዎች በቦርዱ ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ ከ3 እንዳይበልጥ ስለመደረጉ፤ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

**በአንቀጽ 21 ስር የተካተቱ ዋና ዋና ማሻሻያዎች፡-** ይህ አንቀጽ አንቀጽ 26 ሆኖ እንዲስተካከል ከተደረገ በኋላ የሚከተሉት ማሻሻያዎች ተደርገዋል፡-

1. የፕሬዚደንቱ፣ ም/ፕሬዚደንቱ፣ አቃቤ ነዋዩ ምርጫ በጠቅላላ ጉባኤ እንዲጸድቅ መደረጉ፤
2. አስተዳደር ቦርዱ የማኅበሩን ዓመታዊ ዝርዝር እቅድ እና በጀት እንዲያጸድቅ መደረጉ፤
3. አስተዳደር ቦርዱ ከ3 ያልበለጡ የተጓደሉ የቦርድ አባላትን እንዲተካ መደረጉ፤

4. የማኅበሩን ህልውና እና አንድነት አደጋ ላይ በሚጥሉ ጉዳዮች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ወስዶ አፈጻጸሙን ለጠቅላላ ጉባኤው ሪፖርት እንዲያቀርብ መደረጉ፤

**በአንቀጽ 23** የማኅበሩ ፕሬዚደንት ስልጣንና ተግባር በማኅበሩ ውስጥ ያለውን ቦታ እና የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት በሚያስችለው መልኩ ዘርዘር ተደርጎ በአንቀጽ 28 ስር እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡

**በአንቀጽ 26 ስር የተካተቱ ዋና ዋና ማሻሻያዎች**

ይህ አንቀጽ ከላይ በቻርተሩ የተደረጉትን ማሻሻያዎች ተከትሎ አንቀጽ 31 ተብሎ እንዲስተካከል የተደረገ ሲሆን በአንቀጹ ውስጥ የሚከተሉት ተሻሽለዋል፡-

1. ዋና ጸሓፊው የማኅበሩ ከፍተኛ ስራ አስፈጻሚ ስለመሆኑ፤
2. ዋና ጸሓፊው በክልላዊ አደረጃጀት ስር የሚገኙ ሰራተኞች በማኅበሩ ህግ መሰረት መተዳደራቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት እንዳለበት፤
3. ዋና ጸሓፊው በክልላዊ አደረጃጀት ስር የሚገኘው የማኅበሩ ስራ በሚገባ መከናወኑን መከታተል፣ መቆጣጠር እና በየጊዜውም ለብሔራዊ አስተዳደር ቦርዱ ሪፖርት እንዲያቀርብ መደረጉ፤
4. የብሔራዊ አስተዳደር ቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ አቅጣጫ የማህበሩን ሒሳብ ማንቀሳቀስ፣ የግዢ ውሳኔዎችን መስጠት ስለመቻሉ፤
5. በክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊዎች ቅጥር እና ስንብት ላይ ውሳኔ መስጠት እንዲችል መደረጉ፤ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

**አንቀጽ 27** የማኅበሩን የገቢ ምንጮችን በተመለከተ ማኅበሩ ከውጭ እርዳታ ጥገኝነት ተላቆ ራሱን ለመቻል የሚያደርገውን ጥረት ለማጠናከር የገቢ አድማሱን ማስፋት ስላለበት የማኅበሩን አላማ እና መሰረታዊ መርሆች በመጠበቅ በንግድ ስራ ተሰማርቶ ገቢ መሰብሰብ እንዲችል በአንቀጽ 32/6 ስር እንዲካተት ተደርጓል፡፡

**ማኅበሩ ከግብር እና ቀረጥ ነጻ እንዲሆን አዲስ አንቀጽ ስለመጨመሩ**

ማኅበሩ የሰብዓዊ ድርጅት እንደመሆኑ በዚህ ቻርተር ከተፈቀዱለት የገቢ ምንጮች የሚያገኘውን ገቢ ሙሉ በሙሉ ለሰብዓዊ ተግባር የሚያውለው በመሆኑ፤ በተጨማሪም ማህበሩ የሚያገኘው ገቢ እና ከውጭ ለሰብዓዊ ድጋፍ የሚያስገባቸው እቃዎች ከግብር እና ቀረጥ ነጻ የሚያስገባ በመሆኑ ይህም መንግስት በጄኔቫ ስምምነት፣ እ.አ.አ በ1946 በውሳኔ ቁጥር 55 በተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ፣ እና በእንቅስቃሴው አለምዓቀፍ ስብሰባዎች ላይ መንግስት ለማህበሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ለመስጠት በገባው ቃልኪዳን መሰረት

በቻርተሩ አንቀጽ 33 ስር ማኅበሩ ከገቢ ግብር፣ ከውጭ ከሚገቡ ዕቃዎች እና በንብረት ላይ ከሚጣሉ ክፍያዎች ነጻ እንዲሆን የተካተተ ቢሆንም የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በረቂቅ ቻርተሩ ላይ በሰጠው አስተያየት ማህበሩ አላማውን ለማስፈጸም ከውጭ በግዢም ሆነ በስጦታ በሚገቡ እቃዎች ላይ ከቀረጥ ነጻ እንዲሆን ያቀረበውን ጥያቄ በመቀበል በረቂቅ ቻርተሩ የተካተተውን በንብረት ላይ ከሚጣሉ ክፍያዎች ነጻ ለመሆን የቀረበውን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ እንዲሁም ማኅበሩ ከገቢ ግብር ነጻ ለመሆን ያቀረበውን ጥያቄ በከፊል በመቀበል ስምምነቱን በመግለጹ አንቀጹ በሚከተለው መልኩ ተስተካክሎ ቀርቧል፡-

<u>ከግብር እና ቀረጥ ነጻ ስለመሆን</u>

1/ማኅበሩ ዓላማውን ለማስፈጸም ከውጪ በግዥም ሆነ በስጦታ በሚያስመጣቸው ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ እና በገቢ ዕቃዎች ላይ ከሚጣሉ ታክሶች ነጻ ይሆናል፡፡

2/ በሌሎች ህጎች ለማኅበሩ የተሰጡ መብቶች እና ጥቅሞች እንደተጠበቁ ሆነው ማኅበሩ ከአባልነት፣ ከውርስ፣ ከስጦታ፣ ከመንግስት ድጎማ እና ከአምቡላንስ አገልግሎት በሚያገኘው ገቢ ግብር ከመክፈል ነፃ ይሆናል፡፡

**በአንቀጽ 30** የቻርተሩን መሻሻል በተመለከተ አንቀጹ አንቀጽ 37 ሆኖ እንዲስተካከል ተደርጎ በንዑስ አንቀጽ 2 ስር በቻርተሩ አንቀጽ 16/9 ስር ያለውን ኃሳብ ወደዚህ በማምጣት እና በማሻሻል ማኅበሩ ቻርተሩን ሲያሻሽል የአለም ዓቀፉ ቀይ መስቀል ኮሚቴ እና የአለም አቀፉ ቀይ መስቀል እና ቀይ ጨረቃ ፌዴሬሽን የብሔራዊ ማኅበራትን ቻርተር ለመመርመር የተቋቋመው ጥምር ኮሚሽን የሚሰጠውን አስተያየት ግንዛቤ ውስጥ እንዲያስገባ በሚል ተካቷል፡፡

## ቅድሚያ ለሰብዓዊነት!